

# ብሶትሽ ብሶቴ!!

ኑሮ መከራ ሆኖ ፤ ከብዶ እንደድንጋይ፤
ውጣ ውሮድ ሆኖ ፤ ለሰው ልጅ ስቃይ፤
እርቃኑን አስኪዶ ፤ ከፈና አሳጥቶ፤
እልህ አስጨርሶ ፤ ፍዳ አስበልቶ፤



**በእንብርክክ አስኪዶ ፤ የሚቀመስ ጠፍቶ፤**
**ብሶቱን እንዳይገልጽ፤ አንደበቱን ዘግቶ፤**
**ከላይ ተቀምጦ ፤ ሌላው አንዱን ረግጦ፤**
**ከጉያው ተጣብቆ ፤ መጥምጦ መጥምጦ፤**
**ጥቂት ተመች ቶት፤ ሌላው አጥቶ ነጥቶ፤**

መዥገር ደም ቀለቡ ፤ መቼ ይለቅና፤
ሽማግሌ ሕጻኑን ፤ ደሙን ይመጥና!!



በኛህ በዚህ ዘመን ፤ ሕጻናት ተርበው፤
መማር ተስኖአቸው ፤ ስርዓት ከፍቶባቸው፤
ቀኑ መሽቶባቸው ፤ ገና ከጠዋቱ፤
ድርግም ብሎጠፍቶ ፤ ዕሃዩ መብራቱ፤
ፍትህ በሌለበት ፤ ሕግ በጠፋበት፤
ዳኝነት ተፋልሶ ፤ ሰው ዋጋ ባጣበት፤
በካቴና አስሮ ፤ ከስርቤት ዶሏቸው፤



ራዕይ እንዳያዩ ፤ ጨለማ ወርሷቸው።
ሲ.ቃ መከራው ውስጥ፤ ገብቶ ሲ.ዳክሩ፤
እነማን ደረሱ ፤ ፈጥነውስ መከሩ?
ጭንቁን ለማስወገድ ፤ ቆርጦ የታገለ፤
ለሕዝቡ የቆመ ፤ አለሁልህ ያለ።

ብሶትሽ ብሶቴ ፣ ጭንቀትሽ ጭንቀቴ፣

ከተራራው ጀርባ ፣ ያለሽው እናቴ፣

እንጨት ተሸክማ ፣ ቅጠሉን በጥሳ፣

መቀነቷን ቋጥራ ፣ ራቧን አስታግሳ፣

ልጆች ቢታመሙ ፣ ዳማ ኬሴ ቆርጣ፣

አምላኳን ለምና ፣ ወደላይ አንጋጣ ፣

ፀሎቷን አድርሳ፣ ጥሩ ቀን ጠብቃ፣

ወገቧን ጠፍራ፣ መቀነቻ አጥብቃ፣



እንጨት ተሸክማ ፣ በጀርባዋ አዝላ፣

ድንጋይ አሳክላ ፣ ክላይዋ ቆልላ፣

መጫሚያ ሳይኖራት ፣ ባዶ እግሯን እየሄደች፣

እንቅፋት ቦድሷት ፣ እንባ እያነባች፣

በነጠላ አብሳ ፣ ተመስገን እያለች፣

ደፋ ቀና ብላ ሁሌ ፣ እየታገለች፣

ረጅሙን ጉዞ ፣ እያውጠነጠነች፣

ባተሌዋ እናት ፣ እንዲያ እያዘገመች፣

ልብሶቿ አልቆቧት፣ ሰውነቷ ከድቷት፣

ተራራ ሸንተረር ፣ ዳገት ሳያግዳት፣



እራቡ በርትቶ ፣ችግሩ ጠንቶባት፣

ሰንበትን ለማክበር ፣ ቡና እንኳ ሳያምራት፣

ችግሩ አወዛውዞ ፣ ከተማ ሲያደርሳት፣

ታክሲ ሲጮህባት ፣ ትራፊክ ሲቆጣት፣

አውቶሞቢል ነጂው ፣ ጥሩንባውን ነፍቶ፣

ይንቀልሽ ይላታል ፣ አንገቱን አውጥቶ፣

ብቅ ከማለቷ ፣ ሁሉ ተጠይፏት፣

ኑሮ ድንጋይ ሆኖ ፣ እንደዚያ ከብዶባት፣

የሰው ግንባር አይታ ፤ ሁሌ ተለማምጣ፤

ፈገግታዋን ሰጥታ ፤ አንዴም ሳትቆጣ፤

አውቶሞቢል ነድተው ፤ ባስፋልቱ ሽር ብለው፤

ውሃውን ረጭተው ፤ አካሏን አልብሰው፤

ሰው መሆኗን ንቀው ፤ ዘወር እንኳ ሳይሉ፤

ይገሰግሳሉ ፤ ዝም ብለው ይከንፋሉ::



ካቻምና ዘንድሮ፤ እድሜ ልኳን ሁሉ፤

እኽኽ እያለች ፤ እንዲያ እያማጠች፤

ለውጥ መቼ መጣ ፤ መቼ ተከበረች፤

ማነው ያስተዋላት ፤ ውሃ እንኳ ያጠጣት፤

ባገሯ ተንቃ ፤ ድህነቱ ወሯት፤

ምጧን እያማጠች ፤ ትንገላወታለች፤

ድርብ ነው ጭቆናው ፤ ትታገለዋለች።

ብሶትሽ ብሶቴ ፤ ጭንቀትሽ ጭንቀቴ፤

ከተራራው ጀርባ ፤ ያለሽው እናቴ፤

አሁን ያሳሰባት ፤ ቤቷ ፈርሶባት፤

እቃ ሳታወጣ ፤ ማደርያ ሳይሰጧት፤

ከመንደሩ ደርሳ ፤ ከቀየዋ ስትገባ ፤

ፈርሶ አገኘችው ፤ ደሳሳ ጎጆዋ ፤

አንገት ማስገቢያዋ ፤ ዞሮ ማረፊያዋ።

ምንድ ነው ነጻነት ፤ የታል እኩልነት?

ልጅ ያሳደገችበት፤ ሁሉን ያየችበት፤

ደጉንም ክፉውን ፤ያሳለፈችበት፤

አለመጠለያ ፤ እንዴት ይፈርሳል ቤት፤

መቼ ተከበረ ፤ ሰብ አዊነቷ፤

የዜግነት መብቷ፤ ኢትዮጵያዊነቷ፤

ከመንደሯ ስትደርስ ፣ እንባዋ አቅርሮ፣

ሃዘኑ ጠንቶባት ፣ ኑሮ ከፍቶ መሮ፣

አንገቷንም ደፍታ ፣ መሬት ስትቆሮቅር፣

እኔ ማነኝ ብላ ፣ ራሷን ስትመረምር፣

ከመሬት ተኝታ ፣ አልጋ እንኳን ሳይኖራት፣

የክረምቱ ውሃ ፣ እያረሰራሳት፣

ተፈጥሮ እንኳ አምሮ ፣ እየፎከረባት፣

ድንጋዩ ጎርብጦ ፣ ጎኗን እየወጋት፣



አላስተኛ ብሎ ፣ እንቅልፍ እየነሳት፣

ኩራዝ እንኳ ፣ የላት ጋዙ ተወዶባት፣

ራሕቡ ጠንቶባት ፣ ሆድ ጊዜ ሳይሰጣት፣

ተቸገረች ብሎ ፣ ለሷ ማን ደረሰ?

ከአጠገቧ ሆኖ ፣ ማነው ያለቀሰ።

ዱሮ ዱሮ ያኔ፣ ብሶቷን የሚነግር፣

ካደባባይ ወጥቶ ፣ ስለሷ የሚያመር፣

የዳመነው ደምኖ ፣ ሰማዩ ሲጠቅር፣

ወጣቱ ነበር ፣ ወጥቶ የሚኮሳተር፣

በኅብረት አንድላይ ፣ ድምጹን አሰምቶ፣

ምድር ቀውጢ ሆና፣ ት/ቤት ተዘግቶ፣

ነበር የሕዝብ ድምጽ ፣ ተሜ ተማሪው፣

ኮስታራ ጠበቃ ፣ ተከራካሪው።

ደርግ እየተኮሰ ፣ በጥይት ሲቆላ፣



ደም እያፈሰሰ ፣ ሕጻናት ሲበላ፣

”በሃይል በትግል ነው ነጻነት የሚገኘው…”

ብሎ እየፎከረ ፣ ጅግና እየዘከረ፣

ግልብጥ ብሎ ወጥቶ ፣ ብሶት የነገረ፣

ያቆራጥ ተማሪ፣ አሁን የት ደረሰ?

የነሱ ጅግንነት ፣ ሕዝብ ያንቀሳቀሰ።

ባልበላ ባልጠጣ ፣ ምግብ ቀርቶብኝ፣

ጅግና እወዳለሁ ፣ እንዲሁ ጥሎብኝ።

ምን ትጠብቃለህ አትነሳም ወይ

የወያኔ አገዛዝ አይበቃህም ወይ!!

ተነስ በወያኔ ፣ አሳየው ክንድህን፣

ጅግና መሆንህን ፣ ኢትዮጵያዊነትህን።

ብሶትሽ ብሶቴ ፣ ጭንቀትሽ ጭንቀቴ፣

ከተራራው ጃርባ ፣ ያለሽው እናቴ፣

መይሳው ከምድረ ስዊድን 2012-12-24